ሚያዚያ 14 ቀን 2001 ዓ.ም

# እየተሥተዋለ እንጅ! ኢ.ሕ.አ.ፓን ለቀቅ፤ ወያኔን ጠበቅ!

ከአያልነሽ

ሰሞኑን በአካባቢያችን በሠነበተው ግርግር እውነትም "የገቢያ ግርግር . . . ለምን ይመቻል" እንደሚባለው ዓይነት በዚህ በተፈጠረ ግርግር መኃል ከግንቦቴዎች ውስጥ መሪ ነኝ የሚሉት አቶ ሙሉነህ ኢዮል አጋጣሚውን ተጠቅመው አንድ ባለ 3 ገጽ ጽሁፍ ፅፈው በድረ ገጽ ላይ መልቀቃቸውን ተመለከትኩ። አቶ ሙሉነህ ኢዮል "ለስሚ መጠሪያ ቁና ሰፉች" እንዲሉ እሳቸውም "ህቡዕ" ገብተው ከሠነበቱበት ብቅ ብለው ሰሞኑን የሚራገበውን ወሬ አስታከው ስለ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አባት መታሠር ለመግለጽ ፈለጉና አቶ አንዳርጋቸውን ያለማንነታቸውና ያለውሎቸው በሬ ወለደ ታሪክ ደርተው ሊያጥልቁላቸው ሞክረዋል። አቶ ሙሉነህ ኢዮል ስለ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ሰብእናና ማንነት በተመለከተ በወርቅ እንቁ ጽፍው ማቅረብ የተከበረ የግል መብታቸው መሆኑን ባውቅም፣ ወያኔ የኢትዮጵያ ታሪክ "አማራዎች የሠሩት የ100 ዓመት" ታሪክ ነው ብሎ በሬ ወለደ ጣቃውን ሲቀድ አብረው ያስተጋቡትንና ሲያጫፍሩ የኖሩትን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን፣ ዛሬ "ዓረበኛና" እንዲያውም በኢ.ሕ.አ.ፓ ገድልና በኢ.ሕ.አ.ፓ ሰማዕታት ስም፣ እንዲሁም በዚህ ኢትዮጵያዊ ተጋድሎ ታሪክ ውስጥ ሊሸበልሏቸው ሲነሱ አቶ ሙሉነህ ኢዮልን <u>እየተሰተዋለ!</u> ማለትን ግድ ብሏል።

አቶ ሙሉነህ ኢዮል "እንደ ሾላ በድንጋይ እንዳይናድ የተፈራለት ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት" በሚል ርዕስ ሥር ሠፊ ቦታ ሰጥተው የ"ዓርበኛ ልጅ" በሚል አቶ ሙሉነህ የሚያውድሷቸው አቶ አዳርጋቸው ፅጌ "የአርበኛ" ልጅ መሆናቸውን ያነሱና ከአቶ አንዳርጋቸው ቤተሰቦች አንዷ ብቻ "ባንዳ" አግብታ ታሪክ እንዳበለሸች ይገልጣሉ አቶ ሙሉነህ - እንዲህም አድርጎ ጨዋታ የለ! "ጨዋታ ሲደራ እናቴ . . . ምን ነበረች" ብሎ እንደሚያወረው ባለጌ ዓይነት ወግ ነው። እንዲያው ለነገሩ አቶ ሙሉነህ "ባንዳ" አግብታ ታሪክ አበላሸች የሚሏት ሰው በግምት የተፈራ ዋልዋ ባለቤት ትሆን ? ወይስ ሌላ ናት? ። አዬ! አቶ ሙሉነህ እንዴት ተቸገሩ ጌታዬ ተደብቆ የኖረ ምስጢር በማጋለጠዎ። መቼም ከእነዚህ "ነፃ" አውጭዎቻችን ዘንድ እኮ ብዙ ነገር ልንሰማ እንችላለንና ልንደነቅ አይገባም። አንድ ቀን ደግሞ ግንቦቴዎችን የኢ.ሕ.አ.ፓ "ወጣት" ሊግ ክንፍ ናቸው ብለው ቢነገሩን ሊያስገርመን አይገባም። ዘመዶቼ! የእነኝህ ሰዎች የረጅም ጊዜ ዕድሜና ታሪክ የተያያዘው፣ ውሎና አዳራቸውም ጭምር እኮ ዛሬ " በመፈንቅለ መንግሥት" ልንገለብጣቸው እያሰብን ነው ከሚሏቸው ከእነ በረከተ ስሞያንና መለስ ዜናዊ ጋር ነበርና! ጨዋታቸው ሁሉ ታሪክ መበረዝና መንጠቅ መሆኑ አያስገረምም።

በ1983 ዓ.ም ወያኔ ወደ አዲስ አበባ ሲገባ ሕ.ወ.ሓ.ት/ወያኔ (የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት) የሚለውን ስም ይዞ መግባት እጅግ ይከብደው ስለነበር 4 ዴዴዎችን አዘሎ እንደገባ የሚታውስ ነው። ከእነኝህ ውስጥ አንዱና ዋና የነበረው ደግሞ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ድርጅት ኢ.ሕ.ዴ.ን ለመሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። ልብ አድርጉ! ኢህዴን እንደ ኦ.ሕ.ዴ.ድ በ1983 ዓ.ም የተሠራ ሳይሆን ከኦ.ህ.ዴ.ድ ቀድም በሎ በ1973 ዓ.ም (እ.ኢ.አቆጣጠር) ከኢ.ሕ.አ.ፓ. ከደተው ወደ ወያኔ በመግባት በሻዕቢያና በወያኔ ሙሉ ድጋፍ በትግራይ ውስጥ የተጠፈጠፈ ድርጅት ሲሆን ስለ ኢህዴን ደግሞ ከአቶ ሙሉነህ ኢዮል የበለጠ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ በተሻለ ሊናገሩ የሚችሉት እውነት አለ። ዛሬ ደግሞ የአቶ አንዳርጋቸው ቀኝ እጅ

የነበረው ታምራት ላይኔ ሲያገለግለው የነበረው አለቃው መለሰ ዜናዊ "ስኳር ሲቅም " አገኘሁት ብሎ ዘብጥያ ሲያወረደው "አዎን ተመክሬ ነበር" ብሎ አመኖ ከ12 ዓመት እስር በኋላ ከአቶ ሙሉነህ ኢዮል አጠገብ ቅርብ ይገኛልና ስለ ኢህዴንና ስለ አቶ አንዳርጋቸው ታሪክም እንደ አቶ ሙሉነህ ኢዮል በሰማ በለው ሳይሆን በቅርበት የሚያውቀውን በቀጥታ መናገር ይችላል ። ዛሬ አቶ ሙሉነህ ኢዮል የአቶ አንዳርጋቸውን እህት "ባንዳ" አግባታ ብለው መሳለቃቸው (እነ ተፈራ ዋልዋ ከወያኔ ጋር ተጣብቀው መክረማቸው) አስቀንቷቸው ካልሆነ በቀር፣ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌም ቢሆኑ ያኔ ከኢ.ሕ.አ.ፓ ከደተው ለወያኔ በአደሩበት ወቅት፣ ወያኔ (<u>"ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ"</u>) ነኝ ብሎ ወደ አዲስ አበባ ሲገባም፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ አባላትን እየጠቆሙ በወያኔ በማስያዝ፣ ኢ.ህ.ዴ.ን ራሱም ከኢ.ሕ.አ.ፓ ጋር ንክኪ ይኖራቸዋል ወይም ነበራቸው ብሎ ያሰባቸውን "በፎረም 84" ስም ለወያኔ እንዲያድሩ ሲያስጨንቅ የነበረ፣ ለወያኔ አናድርም ያሉትንም ቀስ በቀስ እያደነ በመግደልና በማስገደል፣ እንዲሁም ደበዛቸው እንዲጠፋ በማስደረግ የተጫወተው ሚና በመቅረጸ-መሰል ተደግፎ በብዙ ሰዎች እጅ ይገኛል። ኢ.ሕ.ዴ.ን ይሄን በማድረጉ በዚህ ሚናው ለወያኔ ይበለጥ ተዓማኒነቱን በማሳየቱ ከወያኔ ጋር ሥልጣን የተጋራና ትልልቅ ቦታ ይዞ እንደነበር ታምራት ላይኔ እንደ ግል የ ጠ/ሚኒስትርነት፣ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ደግሞ የአዲስ አበባ ም/ከንቲባነቱን ቦታ ይዘው ወያኔን ሲያገለግሉ እንደነበር ለመካድ፣ ሌላው ቢቀር የአዲስ አበባ ሕዝብ እያንዳንዱ ሞቶ እስኪያልቅ መጠበቅ ሊጠይቅ ነው። ቀድሞውኑም ለንደን ከተማ ውስጥ አቶ አንዳርጋቸው የሚታወቁት ከተማው ውስጥ ባለው የወያኔ ጽ/ቤት ተመላላሽነትና አገልጋይነት ነበር። ለመሆኑ የኢህዴኑ ዋና ሰውና የአቶ አንዳርጋቸው የቅርብ ጓደኛ የነበረው በረከተ ስሞዖንምስ ምን ይል ይሆን? እስከአሁን ነፍሱ አለና የፍትሕ ፀሐይ በሀገራችን ስትወጣና የመጠየቂያው ወቅት ሲደርስ የሚናገረው ይኖራል። የኢትዮጵያ ሕዝብም የአቶ አንዳርጋቸው ፅጌን ማንነትና ድርጅታቸው ስለነበረው ኢ.ህ.ዴ.ንም ከአቶ ሙሉነህ ኢዮል የበለጠ በተግባሩ በዓይኑ በበረቱ የተመለከተው ነውና ሕዝብ መናቅ ልምዳቸው የሆኑ ግለሰቦች ሐሰትን ስለደጋገሙት ታሪክ ተኖ ይጠፋል ማለት አይደለም። አቶ ሙሉነህ ኢዮል ዛሬ በዚህ በሰሞኑ የወሬ ግርግር ቱማታ ተንጠልጥለው አገረ ያወቀውን ፀሃይ የሞቀውን የከረመና የሚጠዘጥዝ ታሪክን በማር ለውሰው አፋችን ውስጥ ሊከቱና ሊግቱን ሲነሱ፣ እንዴት እንዴት ነው ነገሩ <u>እየተስተዋለ እንጅ!</u> ማለት ለነገ የማይበል ግዴታ ሆኗል። ሰማእታትን፣ እንዲሁም አሁንም ታሥረው ደበዛቸው የጠፋብንን ጓዶቻችንን በተመለከተ አሁንም ደግመን ደጋመን ማስታወስ የምንሻው እያንዳንዳችን ሞተን ካላለቅን በቀር (ይሄ ደግሞ አይሆንምና) ማንም በገድላችንና በታሪካችን የፖለቲካ ንግድ ሊነገድ ሲነሳ የማንፈቅድለትና በዝምታ ልናልፈው የማንችል ጉዳያችን መሆኑ እንዲታውቅ ነው።

ሠማዕታትንና የሠማታትን ገደል በተመለከተ ደግሞ እንኳንስ በስማ በለው ወሬ ተነሥተው ዘራፍ እያሉ አገር አልበቃቸው ያሉ ግለሰቦች ሊነግዱባቸው ቀርቶ፣ በእውን የገደሏቸውንና ያስገደሏቸውንም ቢሆን ወያኔ ሊዳኝ ሲነሣና ለራሱ ርካሽ ፓለቲካ ሊጠቀምበት ሲሞክር (ያኔ የሰማእታታችንን ሬሣ እየቆፈረ ሲያላቅስ ) ቶሽ! አቁም - በማለት ግንባር ቀደም ሆኖ መሪር ተቃውሞውን ያሰማው ኢ.ሕ.አ.ፓ እንደነበር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስውር አይደለም። በተደጋጋሚም ኢ.ሕ.አ.ፓ ይህንን ሰቅጣጭ የሆነ የወያኔን ድርጊት አውግዞ በአስቸኳይ እንዲያቆመውና እጁንም እንዲሰበስብ በራዲዮዎው ሳይቀር አስጠንቅቆ ነበር። በነገራችን ላይ ወያኔ ይሄንን ሰቅጣጭ የሆነ ቲያትሩን በኢትዮጵያ ውስጥ በአደባባይ በቀይ ሽብር

የተገደሉ ሠማዕታትን ጉዳጓድ እየቆፈረ፣ እናቶችንና አባቶችን በሚስያስለቅስበት ጊዜ በአንፃሩ ከዚህ ሽብር የተረፉትን ኢ.ሕ.አ.ፓዎችን ደግሞ ወያኔ በኢ.ሕ.ዴ.ን አማካኝነት ያድን ነበር፣ እኛም ይሄንን እያደረገ ባለበት ወቅት ያኔ በወያኔ እስር ቤት ታጉረን መከራ እናይ እንደ ነበር የአቶ አንዳርጋቸው ድርጅት ኢ.ሕ.ዴ.ን ያውቃል። እጅግ በጣም የሚያመው ደግሞ ወያኔ ይሄንን በሰማዕታት ላይ ሊሠራ የሞከረውን ዘገናኝ ቲያትር በምናስብበት ጊዜ እነ ፀጋዬ ገ/መድኅን (ደብተራውንና) ሌሎች ጓዶቻችን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አስሮ እያለ እስካሁን ድረስ የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ብሎ አላያሁም አለሰማሁም ብሎ 18 ዓመት አፉ ተሸብቧል። ታዲያ አቶ ሙሉነህ ኢዮል ያልበላቸውን ሲያኩ የዛሬ 30 ዓመት በኢ.ሕ.አ.ፓነት በቀይ ሽበር የተገደሉ ጀግኖችን እያነሱ አቶ አንዳርጋቸውን የዚያ ታሪክ ባለቤት ሊያደርጓቸው ብዙ ጎንበስ ቀና ማለታቸውን ሳይ እጅግ አዘንኩ። አቶ ሙሉነህ የዚህ ታሪክ ባለቤት ሊያደርጓቸው ያሰቡትን አንዳርጋቸው ፅጌን ይህን የሳቸውን ልፋትና ድካም በበጎ ካዩላቸውም አንድ ነገር በሆነ። የሚያሳዝነው ግን አቶ አንዳርጋቸው ደግሞ ከወያኔ በላይ በቁጥር 1 የሚጠሉት ድርጅት ቢኖር ይሄው ኢ.ሕ.አ.ፓ. ለመሆኑ እነ ፀጋይ /ደብተራውን ምስክርነት መጠራት አያሻም።

አቶ ሙሉነህ ኢዮል ጨዋታ አሳመርኩ ብለው ከ"እናቲቱ ሞግዚቲቱ" በመሆን ስለ አቶ አንዳርጋቸው ቤተሰብም ብዙ ሊያወሩ ፈለገው ነገር ግን ከጀመሩት ወግ ተስፈንጥረውና ለቀው በመውጣት አቶ አዳርጋቸው ከምር የሚጠሉትን ኢ.ሕ.አፓንና ኢ.ህ.አፓዊ ታሪክ በሟቹ ወንድማቸው አድርገው ሊያላብሷቸው መከራ ሲያዩ ይታያል። እንዲህ ዓይነቱ ወግ መሬቱ የሚያበቅለውን ዘር ሳይሆን ገበሬው የሚፈልገውን እንደበተነው እህል ዓይነት ወለፈንዲ ሊባል የሚችል ነው። እንደ እውነቱ፣ እውነት ይነገር ከተባለ ግን ያኔ ያኔ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደርጅትና ፓርቲ የነበረውና የሆነው ኢ.ሕ.አ.ፓ፣ ሀገር አቀፍና ህብረ ብሔራዊ ድርጅት ስለነበረ በኢ.ሕ.አ.ፓነት ተሠልፈው፣ ሞትን ንቀው፣ እኔ ልቅደም እኔ በማለት ከሞት ጋር እሽቅድምድም ይዘው የሕይወት መስዋዕትነት በመክፈል ኢትዮጵያዊ ጀግንነትን በደማቸው የፃፉ ባለታሪኮች በሙሉ፣ ከኤርትራ ጠ/ግዛት ጀምሮ እስከ ዳር አገር ሞያሌ ድረስ በ14ቱ ጠ/ግዛት ውስጥ የተወለዱና ያደጉ ኢትዮጵያዊ ጀገኖች ለመሆናቸው እንኩዋንስ ሕዝባችን የኢ.ሕ.አ.ፓ ጠላት ሆነው የቆሙትም ይመሰክሩታል።

በኢትዮጵያ ምድር የኢ.ሕ.አ.ፓ አፅም ያልተቀበረበት መሬት ተፈልጎ አይገኝም። የኢ.ሕ.አ.ፓ አባላት/አባል ያልታሠረበት/ያልታሠሩበት እስር ቤቶች በኢትዮጵያ ምድር የለም። የኢትዮጵያ ምድር ቢቆፈር አብዛኛው ጉድጓድ የኢ.ሕ.አ.ፓን አፅም የተሸከሙ ለመሆናቸው ምስክሮች ናቸው። ኢ.ሕ.አ.ፓ በኤርትራ፣ በትግራይ፣ በወሎ ፣በጎንደር፣ በጎጃም፣ በሸዋ፣ በወለጋ፣ በኢሉባቡር፣ በከፋ፣ በጎምጎፋ፣ በሲዳሞ፣ በባሌ፣ በአሩሲ፣ በሀረርጌ፣ በ14ቱ ክ/ሀገር ያልታሠረበት፣ ያልተገደለበት፣ ያልተቀበረበት አፈር አይገኝም። እንኳን የኢትዮጵያ ምደር ቀርቶ በሶማሊያና በሱዳን ምድር ውስጥ የሚገኙት እስር ቤቶች ስለ ኢ.ሕ.አ.ፓ አፍ አውጥተው መናገር ቢችሉ የሚናገሩት ብዙ ያልተነካ ታሪክ አላቸው። ይሄ እውነት ነው። ይሄ ደግሞ የኢ.ሕ.አ.ፓ አባላትና የኢ.ሕ.አ.ፓ ደጋፊዎች የሆኑ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሞላ ሠራተኛው፣ ላባደሩ፣ አርሶ አደሩ፣ ወታደሩ፣ አስተማሪው፣. ተማሪው፣ ሴቶች፣ በእናቶች የተቋቋመውን(የኡኡታ ኮሚቴ) ማን ይረሳዋል? ይህ ብቻ አይደለም፥ ገድላቸውም ለለውጥ፣ ያውም ለመሠረታዊ ለውጥ፣ ለኢትዮጵያ

መሠረታዊ ዕድገት፣ ብልጽግና፣ ለዜጎች እኩልነትና በእኩልነት ላይ ለተመሠረተም ኢትዮጵያጵያዊ አንድነት ሲሉ ነው።

ደግሞም በፍላጎታቸው (እንዳዘሬው "ነፃ" ልናወጣህ 500 ክፍል) ሳይባሉ ራሳቸው ከገንዘብ በላይ ውዱን ሕይወት ከፍለው በመስዋዕትነት በተግባር ያሳዩና በጠላቶቻቸውም ሳይቀር የተደነቁ ጀግኖች ለመሆናቸው ሩቅ መሄድ አያስፈልግም፤ ታሪኩ በቁመና የሚገኘው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። በኢ ት ዮ ጵ ያ ምድር!

- እስቲ! ይፈቀድለት እንዲናገር የኢትዮጵያ መሬት !
- እስቲ! ይፈቀድላት እንድትናገር ዕድሜ ልክ ወደ ውስጧ እያነባች ያለችው የኢትዮጵያ እናት!
- እስቲ! ይፈቀድለት እንዲናገር በሽብር የተበተነው ቤተሰብ!
- እስቲ! ይፈቀድላቸው እንዲናገሩ በአንድ ጉድጓዳ ውስጥ ተደራርበው የተቀበሩ ሬሣዎች!
- እስቲ! ይፈቀድላቸው እንዲናገሩ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩት የተቆራረጠ የሰው አካላት ሲበሉ የደለቡ የዱር አራዊቶች!
- እስቲ ይፈቀድና እንናገር/እናልቅስ በኢትዮጵያ ምድርና ህዝብ መሐል ሆነን ከኢትዮጵያ እናቶች ጋር . . .
- በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ይፈቀድ እስቲ ሁላችንም በነፃ እንድንናገርና እንድናውራ!
- እስቲ! ይፈቀድ በሃገራችን ያለፍርኃት በነፃነት ማውራት!. . . . ይፈቀድ! ይፈቀድ! ይፈቀድ! እና እንተያይ! እንደዚያ አይሻልም። አለበለዚያ " ሳይገደሉ ጎፈሬ፣ ሳያጣሩ ወሬ" ዓይነቶች የዓለምን ምድር ይሞሏታል።

"ዶሮ ጭራ፣ ጭራ ማረጃዋን አወጣች" ይባላል። ዛሬ ኢትዮጵያን የባለ "100" ዓመት ታሪክ ተረት ተረት ፈጥሮ ከመነሻው ጀምሮ እስከ አሁን በመቶ ሽዎች የሚቆጠር የሰው ሕይወት እየቀጠፈና አሁንም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በመቀጠፍ ላይ የሚገኘው ወያኔ፣ አሁን ለደረሰበት ሥልጣን የበቃው በወያኔ የተሠራውን በሬ ወለደ ተረቱን እነ ኢ.ሕ.ዴ.ን (የአቶ አንዳርጋቸው ድርጅት) ከጫካ ጅምሮ ተቀብለው እንደ በቀቀን በማስተጋባት፣ አዲስ አበባም ከገቡ በኋላም በመጽሐፍ <u>*"የአማራው ሕዝብ ከየት ወደየት"*</u> ብለው የፃፉልንንስ የ"አርበኘነት" መጽሃፍ እንበልላቸው አቶ ሙሉነህ?

እስቲ ስለ አቶ አንዳርጋቸው ዕጌ የ "አርበኛ" ልጅ መሆን አቶ ሙሉነህ ኢዮል ከሚጽፉ ይልቅ እባክዎን! ኢ.ድ.ሊ ስለሚባለው ቁንጫ የሚፃፍ ነገር ካለ ይልቅ ከቁንጫ ማጥፊያ መደኃኒቱ ጋር ጽፈው ይዘዙልንና እንግዛ! በተረፈ ግን ኢ.ሕ.አ.ፓን ለቀቅ ወያኔን ደግሞ ጠበቅ! ነው።

ነገሬን በዚህ ልቋጨው . . . .

*ቁንጫን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ አለ? መቼም ይህንን ተባይ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ያውቀዋል ብዬ እገምታለሁና የቁንጫ ዋና ባህሪ ደግሞ የማይያዝ፣ የማይጨበጥ፣ ሊይዙት ቢሞክሩም ተሰፈንጥሮ በርሮ ይጠፉና እንደገና ሳይታይ ተመልሶ በሰዎች*

*አካላት ላይ ሰፍሮ ደም እየመገመገ ህይወቱን የሚያኖር ተባይ ነው። ቁንጫ ? መጥፎ ተባይ!*

**የህዝብ ድምፅ ይከበር! የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!**
**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**
**ቼር ይግጠመን**
**ሜይ** 2/ 2009